የሰ/መ/ቁ. 33841

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አስጨናቂ ረጋሣ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ ወኪል ሙሉመቤት - ቀረቡ

2. ወ/ሪት ሙሉእመቤት ነጋሽ - ቀረቡ

3. ወ/ሪት አሰገደች ነጋሽ - አልቀረበችም

4. አቶ ዘላለም ነጋሽ

5. አቶ ዳኛቸው ነጋሽ ወኪል - ቀረቡ

6. አቶ ኤፍሬም ነጋሽ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥሰናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወረሰና አባታችን ከአዋጁ በፊት በወለድ አግድ አስይዞት የነበረ፣እንዲሁም በቅጽ 004 የተመዘገበ የአባታችን አቶ ነጋሽ መንገሻ ንብረት የሆነ ቁጥሩ 668/669 ቤት አመልካችና የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት በፍርድ ተገድደው እንዲያስረክቧቸው ለአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ነው፤ በማስረጃነት የቀረበው ቅጽ 004 በሚመለከተው የበላይ አካል ያልፀደቀና በቀበሌ ደረጃ ብቻ የተሞላና አስተያየት የተሰጠበት ሰነድ በመሆኑ ቤቱ ያልተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት አይቻልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፤ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው በማለት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ቤቱ በቅጽ 004 የተሞላ ተጠሪዎች አውራሽ የምርጫ ቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለ በመሆኑ ለተጠሪዎች መመለስ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኛት ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፤ በመጀመሪያም የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረ-ነገር ስልጣን የለውም፤ ቤቱ የተወረሰ ነው፤ ቅጽ 004 የተባለው በሚመለከተው አካል የፀደቀ ባለመሆኑ ቤቱ ለተጠሪዎች አውራሽ በምርጫ ቤትነት እንዲይዙት የተወሰነ መሆኑን ለማስረዳት ብቃት የለውም፤ የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ ቤቱ በቅጽ 004 በወቅቱ ሕጋዊ ስልጣን ባለው አካል ለአውራሻችን በምርጫ ቤትነት የተሰጠ ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ስህተት የለበትም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለማየትና ቤቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወሰረ በመሆኑ ለተጠሪዎች ይመልስ በማለት የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውመሰረታዊ የህግ ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ሐላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም የምንረዳው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማ አስተዳዳር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ሆኖም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው ወይስ የሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ በተጠሪዎች በኩል ክርክር እያቀረቡበትና የጉዳዩም መሰረታዊ ጭብጥ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ተወርሷል ወይስ አልተወሰረም የሚል በመሆኑ ይህንን ጉዳይ ሰምተውና አከራክረው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችላቸው የሥረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0455 ጥር 5 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የሥረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጡ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድብባቸውም ብለናል፡፡
3. በትውስት የመጣው መዝገብ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ ስለሆነ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ